መራዱ ላዕሌሁ ወትጼውዮን ለኃጣውኢሁ ከመ ይሩዳሁ ወይዑዳሁ ከመ ማዕገት ጽፉቅ።ወእምዝ ይጼውኣ ለምሕረት ወኢትሰጠዎ እስመ ኢገብረ ምሕረተ ለዘይትጋነይ ሎቱ።የኀሥሣ ለማህል ወኢይረክባ እስመ ኢኀለየ ማህለ ለቍሱላን ።አንትሙኒ አበዊነ ወአኃዊነ ለእመ ሐፀበክሙ እገሪክሙ ካህን በከመ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን አንትሙኒ ሕፅቡ ልበክሙ በየውሃት ወእደዊክሙ በውሂበ ምጽዋት፡ አንጽሑ ሥጋክሙ ወነፍስክሙ ከመ ትኩኑ ድልዋነ ለተዝካረ ሕማማቲሁ ለክርስቶስ ሎቱ ስብሐት ለዓለመ ዓለም። አሜን።

............ /// ............

ዘንድ ኃጢአቶቹን ትጠራቸዋለች ከዚህም በኋላ ይቅርታን ይጠራታል አትመልስለትም ይቅርታ ለጠየቀው ይቅርታን አላደረገምና ይቅርታን ይፈልጋታል አያገኛትም ለቁስለኞች ይቅርታን አልሰጠምና። እናንተም አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ሆይ ካህኑ እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እግራችሁን ካጠባችሁ እናንተም ሥጋችሁን በእንባ ምንጭ እጠቡ ሁለተኛም ልባችሁን በገርነት እጃችሁንም ምጽዋት በመስጠት እጠቡ ለክርስቶስ የመከራዎቹ መታሰቢያ የተዘጋጃችሁ ትሆኑ ዘንድ ሥጋችሁንና ነፍሳችሁን አንጹ ለእርሱ ምስጋና ይገባል ለዘላለሙ አሜን።

............ /// ............